# መጽሐፍ ቅዱስ ለህፃናት
## አቅራቢዎች



እግዚአብሔር ባሪያውን ዮሴፍን አክብሮታል

ጸሐፊው: Edward Hughes
ምሣሌ አቅራቢው: M. Maillot; Lazarus
ያሻሻለው (አሻሻሎ የጻፈው): M. Maillot; Sarah S; Alastair P.
የተተረጎመው: Eyerusalem Dechasa
አዘጋጅ: Bible for Children
www.M1914.org

BFC
PO Box 3
Winnipeg, MB R3C 2G1
Canada

©2020 Bible for Children, Inc.
ፈቃድ፤- ይህንን የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ ማባዛት ወይም ማተም ይቻላል ነገር ግን ይህ መሆን የሚችለው ለሽያጭ ካላቀረባችሁ ብቻ ነው።

ዮሴፍ በቀድሞው ጌታው ጲጢፋራ ባላጠፋው ጥፋት በእስር ቤት ነበረ። ዮሴፍ በእስር ቤት ታዛዥና ሰዎችን የሚረዳ ነበር። የእስር ቤቱ ተቆጣጣሪ ዮሴፍ የእስር ቤቱን ህይወት ለማደራጀት እምነት አሳደረበት። እግዚአብሔር ከዮሴፍ ጋር ስለነበረ እስር ቤት ለሁሉም ሰው የተሻለ ቦታ ሆነ።




የንጉሡ ዳቦ ጋጋሪ እና የእልፍኝ አሽከር
በእስር ነበሩ. "ለምን አዝናችኋል?"
ዮሴፍ አንድ ቀን ጠየቃቸው።
የተጨነቁ ሰዎች "ማንም ሰው ሕልማችን
ምን ማለት እንደሆነ
ሊያሳየን
አይችልም"
ብለው
መለሱ።
"እግዚአብሔር ይችላል!"
ዮሴፍም "ሕልማችሁን
ንገሩኝ" አላቸው።



"ሕልምህ በሦስት ቀናት ውስጥ ወደ ንጉሱ ፈርኦን ዘንድ ትመለሳለህ ማለት ነው" ብሎ ለእልፍኝ አሸከሩ ነገረው። በተፈታህ ጊዜ "አስታውሰኝ እናም ፈርዖን እንዲፈታኝ ጠይቅልኝ" አለው። የዳቦ ጋጋሪው ህልም መጥፎ ዜናን ይዞ ነበር። "በሶስት ቀን ውስጥ ትሞታለህ" የሚል ነበር። ሁለቱም ሕልሞች እውን ሆኑ።

ነገር ግን የእልፍኝ አሽከሩ ዮሴፍን ረሳው።
ፈርኦንን አንድ ቀን ከእንቅልፉ ሲነቃ ተረብሾ
ነበር። "ሕልም አይቼ ነበር" እያለ
ጮኸ። ሆኖም ግን ከጠቢባኑ
መካከል
አንዳቸውም
ትርጉሙን





ሊያሳዩት
አልቻሉም።
በድንገት የእልፍኝ አሽከሩ
በእስር ቤት ያለውን ዮሴፍን
አስታወሰው። ለፈርዖንም ስለ
እርሱ ነገረው።

ፈርዖንም ወዲያውኑ ወደ ዮሴፍ ላከበት።
"ሕልም ከእግዚአብሔር የመጣ መልእክት ነው"
በማለት ዮሴፍ ለንጉሡ ነገረው። "ግብፅ ሰባት
ዓመታት የተትረፈረፈ እህል, ከዚያም ሰባት
ጥማትና ረሃብ ይኖርባታል." አለው።



ዮሴፍም ፈርዖንን "በሚመጡት
በሰባቱ መልካም አመታት እህል
ለማከማቸት እቅድ አውጡ
ይህካልሆነ ግን ህዝቦችህ
እስከሞት ድረስ
ይራባሉ" ሲል
መከረው።
ፈርዖንም
"እግዚአብሔር
ከእናንተ ጋር
ነው ከእኔም
በኋላ በግብፅ
ላይ ትነግሳለህ"
አለው።



ሰባቱ የጥጋብ ዓመታት መጡ። ከዚያም በኋላ ሰባት የረሃብ ዓመታት ተከተሉ። በሁሉም ሀገር የምግብ እጥረት ተከሰተ። በግብፅ ግን ብዙ ምርቶችን አከማችተው ስለነበር አልተራቡም።

የያዕቆብ ቤተሰቦችም ተርበው ነበር።



ከተለያዩ አገሮች የመጡ ሰዎች እህል ለመሸመት ወደ ግብጽ ሄዱ። ያዕቆብም ልጆቹን "እናንተም ለመሸመት መሄድ አለባችሁ ካልሆነ ግን እስክንሞት ድረስ እንራባለን" ሲል አዘዛቸው።

ግብፅ እንደደረሱም እህል ለመሸመት መዘጋጀት ጀመሩ።



የያዕቆብ ልጆች በግብፅ ላይ በተሾመው ጌታ ፊት ለፊት ሰገዱ። እነሱም ወንድማቸውን ዮሴፍን አላውቁም ነበር። ነገር ግን ዮሴፍ አወቃቸው። ዮሴፍም ባያቸው ጊዜ የልጅነት ህልሞቹን አስታወሰ። እግዚአብሔር ከወንድሞቹ በላይ ከፍ አድርጎታልና።



ዮሴፍ በጣም ጥበበኛ ስለነበር እንደማያውቃቸው ሆኖ አናገራቸው። "እህሉን ወስዳችሁ ወደ ቤታችሁ ሂዱ። ነገር ግን ስትመለሱ ታናሽ ወንድማችሁን ይዛችሁ ተመለሱ በዚህም ሰላዮች እንዳልሆናችሁ አረጋግጣለሁ"



ብሎ አዘዛቸው።

ለዚህም ደግሞ ወንድማቸውን ስምኦንን በመያዝ እሱ ጋር አስቀረው። ወንድሞቹም ከብዙ አመታት በፊት ዮሴፍን እንደባሪያ በመሸጣችን እግዚአብሔር እየቀጣን ነው ብለው አሰቡ።



ያዕቆብ እና ልጆቹ ግራ ተጋቡ። "ገንዘቦቻችንን በስጠን እህል ውስጥ ተመልሶ አገኘን። እናም ወንድማችን ብንያምን ማምጣት እንዳለብን ግድ አለን "ብለው ለያዕቆብ ነገሩት። ያዕቆብ ግን ብንያም እንዲሄድ አልፈቀደም። ሆኖም ግን ብዙም ሳይቆይ ምግቡ አለቀባቸው። ስለዚህም ወደ ግብፅ መመለስ ነበረባቸው። ብንያምም ከእነርሱ ጋር አብሮ ሄደ።



ዮሴፍም ብንያምን ባየው ጊዜ አገልጋዮቹን ትልቅ ግብዣ እንዲያዘጋጁ አዘዛቸው። ወንድሞቹም ተጋብዘው ነበር። "አባታችሁ ደህና ነው?" ሲል ዮሴፍ ጠየቃቸው። ምናልባትም ሁሉንም ቤተሰብ እንዴት ሊያመጣ እንደሚችል እያሰበ ሊሆን ይችላል።



ዮሴፍ ወንድሞቹ ከብዙ አመታት በፊት በሠሩት ኃጢኣት በ በእውነት አዝነው እንደሆነ ለማወቅ ፈልጓል። ከግብዣው በኋላ ዮሴፍ ወንድሞቹን በስርቆት ወንጀል ከሰሳቸው። ዮሴፍም "እናንተን ለመቅጣት ብንያምን እንደ ባሪያ አድርጌ ወሰደዋለሁ" አላቸው።



ይሁዳም "ጌታዬ ሆይ, በእሱ ፈንታ ነፍሴን ውሰድ" ብሎ ለመነው። ዮሴፍም እሱን ለመሸጥ ሐሳብ አቅርቦ የነበረው ይሁዳ በእውነትም እንደተለወጠ አየ።



ዮሴፍም ከዚህ በላይ ለቤተሰቡ ያለውን ፍቅር መደበቅ አልቻለም። ስለዚህም በቤት ውስጥ የነበሩት ግብፃውያን በሙሉ አስወጥቶ ማልቀስ ጀመረ። "እኔ ወደ ግብፅ የሸጣችሁኝ ወንድማችሁ ዮሴፍ ነኝ" አላቸው። ወንድሞቹም መደነቅና ፍርሃት ተቀላቅሎባቸው ምንም መናገር አልቻሉም።

ዮሴፍ ወንድሞቹን እንዲህ ሲል አበረታታቸው "እግዚአብሔር ሕይወታችሁን በዚህ



የረሀብ ጊዜ አድናት ዘንድ በግብፅ ምድር ላይ ጌታን አድርጎ ሾመኝ። ሂዱና አባቴን አምጡ; እኔም እከተላችኋለሁ" አላቸው።



ያዕቆብና ዮሴፍ
በግብፅ እንደገና ተገናኙ።
ከዚያም ሁሉም ቤተሰብ
በሰላምና በተትረፈረፈ
ህይወት መኖር ጀመሩ።

እግዚአብሔር ባሪያውን ዮሴፍን አክብሮታል

ይህ ታሪክ የሚገኘው የእግዚአብሔር ቃል
በሆነው መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ

ኦሪት ዘፍጥረት 39-45

“የቃልህ ፍቺ ያበራል.”
መዝሙረ ዳዊት 119:130

# መጨረሻ

ይህ የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ የሚያስተምረን ግሩም ስለሆነው አምላካችን
እግዚአብሔር እኛን በመፍጠሩ እሱን እንድታውቀው ነው።

እግዚአብሔር “ኃጢአት” ብሎ የሚጠራውን ክፉ ነገር እንዳደረግን ያውቀዋል።
የኃጢአት ደመወዝ ሞት ነው ነገር ግን እግዚአብሔር በጣም ስለወደደን
አንዱንና ብቸኛው ልጁን ለቀራኒዮ መስቀል ሞት አሣልፎ በመሥጠት
እንዲሞትና የኃጢአታችንን ዋጋ በእኛ ምትክ በመሞት እንዲከፍል አደረገው።
ኢየሱስ ከሞት ከተነሣ በኋላ በምድር ላይ ቆይቶ ወደ ሠማይ ወደ አባቱ አረገ!
ያላመንን እኛም በኢየሱስ አዳኝት ብናምን እና ኃጢአታችንን ይቅር እንዲል
ብለምነው ይቅር ይለናል። ደግሞም ያደርገዋል። እሱም በእኛ ውስጥ ይኖራል፤
እኛም በእርሱ ውስጥ ለዘላለም እንኖራለን አሜን።

ይህ እውነት እንደሆነ ካመናችሁ፣ እግዚአብሔርን እንዲህ በሉት
ጌታ ኢየሱስ ሆይ አንተ አምላክ እንደሆንክ አምናለሁ ነገር ግን ለእኔ ኃጢአት
ለመሞት ስትል ሰው ሆንህ አሁን ደግሞ ህያው ነህ። እባክህ ወደ ህይወቴ ግባ
ኃጢአቴን ይቅር በል በዚህም አዲስ ህይወት አሁን ይኖረኛል አንድ ቀን
ከአንተ ጋር ለዘልዓለም ለመኖር ወደ አንተ እመጣለሁ። ለአንተ እንድኖርና
እንደ ልጅ እንድታዘዝልህ እርዳኝ። አሜን።

በየዕለቱ መጽሐፍ ቅዱስን በማንበብ ከእግዚአብሄር ጋር ተነጋገር! የሐ. 3.16